‹‹አራት ዓመት በሃኪም ቤት፣ 9 ዓመት በአልማ የቤተሰብ ምጣኔ አግልግሎት ተጠቃሚ ነን። እኔ በግለሰብ ቤት ውስጥ በ60 ብር ተቀጥሬ ነበር የምሰራው። ያኔ ትልቋ ልጅ ተወለደች። እሷን ለማሳደግ ተቸግረናል። ለክርስትናዋ እንኳን መደገሻ አጥተናል። በዚህ ምክንያት ሁለተኛ መድገምንም እንኳን አልመኘም ነበር። ነገር ግን ተወለደች። በሃኪም ቤት እገዛ ሦስተኛ እንዳይወለድ አድርገን ቆየን።

‹‹እስከ ዛሬ ድረስም ገቢያችን ትልቅ ነው የሚባል አይደለም። ልጅ አለማብዛታችን ግን እንድንቆጥብ አድርጎናል። አሁንም በ100 ብር ደሞዝ የገበሬዎች አግልግሎት ጽ/ቤት የጥበቃ ሠራተኛ ሆኜ ነው የምኖረው። በመቆጠባችን ግን በጎች ገዛን። አንዲት ላምም አለችን። ወርልድ ቪዥንም ሌላ ላም ሰጠን።

‹‹ልጆቻችን አይራቡብንም። አይራቆቱብንም። በምግባቸውም ሆነ በልብሳቸው አቅማችን በሚፈቅደው መጠን እንንከባከባቸዋለን። ሁለት ስለሆኑና በደንብ ስለምንይዛቸው በአመጋገብ ጉድለት ወይም በኑሮ ጉስቁልና የሚመጣ ህመም የለባቸውም። ጤነኞች ናቸው። የአዕምሮ ጭንቀት የለባቸውም። ሰውነታቸውም የተጎዳና የከሳ አይደለም።

‹‹ልጆቻችንን እያስተማርናቸውም ነው። ትልቋ ብዙዬ ትባላለች። የ7ኛ ክፍል ተማሪ ነች። ትንሿ ሰላም ደግሞ 6ኛ ክፍል ደርሳለች። ትምህርታቸውን አቋርጠው አያውቁም። የትምህርት መሳሪያ አይቸግራቸውም፤ እኛው ነን አሟልተን የምንገዛላቸው።

አቶ መኮንን ታዬ

ወይዘሮ ቀለሚ አበበ
ከሰሜን ሸዋ ዞን፣ አንጎለላና ጠራ ወረዳ፣ ኮቱ ቀበሌ

‹‹የአሁኑ ባለቤቴ መውለድ ይፈልጋል፡፡
‘እነዚህን ለቁምነገር ሳብቃ›
ብዬ ስነግረው ያደምጠኛል፡፡

‹‹ሁለት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች አሉኝ። አምስቱም ይማራሉ። ሁለቱ ዘንድሮ (2001 ዓ.ም) የ10ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ጨርሰዋል። አንዱ 7ኛ፣ አንዷ 5ኛ ናቸው። ትንሹ የ2ኛ ክፍል ተማሪ ነው። ሁሉም ትምህርታቸውን አቋርጠው አያውቁም።

‹‹ድሮ የ8ኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ጠልፎ የወሰደኝ ባል ነበረኝ። እነዚህን አምስቱንም ልጆች ከእሱ ነው የወለድኳቸው። አከታትዬ ስለወለድኳቸው ሰውነቴ እየኮሰሰ ይሄድና እደክም ነበር። ባለቤቴ ግን ከዚህም በላይ ብጨምርና አስርም ብወልድ ስለሚፈልግ ጣጣ አልነበረውም። ሴት ልጅ መቀጫዋ አከታትሎና አብዝቶ መውለድ ነው። የምጐዳው እኔ ነኝ። እሱ ምኑ ተነካ!? በዚያ ላይ ጠጪና ሰካራም ስለነበረ በፍርድ ቤት ተፋታንና ሌላ አገባሁ።

‹‹የአሁኑ ባለቤቴ መውለድ ይፈልጋል። ‘እነዚህን ለቁምነገር ላብቃ› ብዬ ስነግረው ያደምጠኛል።

‹‹የተዋልዶ ጤና አግልግሎት ተጠቃሚ መሆን የጀመርኩት አልማ ከመጣልን ጀምሮ ነው። ዘጠኝ ዓመት ሆነኝ። ከራሴ ተርፎ ሌሎችንም እየመከርኩኝ ተጠቃሚ ሆነው ወደ ምርት እየተሰማሩ ነው።

‹‹አሁን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን! ጤነኛ ነኝ። ወደ ሥራም እሰማራለሁ። የግብርና ሥራና ከብት ማርባት እሰራለሁ። እነግዳለሁም። ጥማድ በሬ አለኝ። የእርሻ መሬት አለኝ። ላሞችና በጎችም አሉኝ። ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም (አብቁተ) እየተበደርኩኝ እየሠራሁ የራሴን ቤት ሠርቻለሁ።

‹‹የአልማ ወኪሎች የሚያስተምሩን ብዙ ነው። አንድ ለአንድ ስለመወሰን፣ ከጋብቻ በፊት የደም ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ያስተምሩናል። የሚነግሩንን ተግባራዊ እያደረግን ነው።

‹‹ይህ የአልማ ጉዳይና የእኛ በትልቁ መጠቀም በመፅሔት ቢወጣ ጥሩ ነው። ለልጆቻችንም መማሪያ ይሆናል። ይህ የአልማ ትምህርት ቀደም ብሎ ቢኖር ኖሮ መልካም ነበር። አልማን ከማንም በላይ የማመሰግነው ድርጅት ነው። የበለጠ ያስፋው፣ ያስፋፋው።››

በደቡብ ወሎ ዞን ተንታ ወረዳ የአልማ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት

መላከ ፀሐይ ወርቅነህ አሰፋ በተንታ ወረዳ 06 ቀበሌ ነዋሪ ናቸው፡፡ በአካባቢያቸው በተዋልዶ ጤና አገልግሎት በተለይም ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችንና የኤች አይቪ ኤድስ ቫይረስ ስርጭትን በመከላከል እንዲሁም በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ዙሪያ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ወክለው ያገለግላሉ፡፡ 16 የጤና ፓኬጆችን በመተግበር በተንታ ወረዳ በሞዴልነት ከተመረጡት አርሶ አደሮች መካከልም አንዱ ናቸው፡፡

መላከ ፀሐይ ወርቅነህ አሰፋ

"ያለዕድሜ ጋብቻ፤ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ግግ ማውጣትና መሰል ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል አስተምራለሁ፡፡ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን በመከላከልና የተመጠነ ቤተሰብ እንዲኖር በማድረግ በኩልም ከአልማ ወኪሎች ጋር በመነጋገር እንዲሁ እሰራለሁ፡፡

ሠርግ፣ ተስካር እየተባለ በሚደረግ ድግስ የኩርቻ በቅሎ፣ የወተት ላም፣ የቀንበር በሬ እንዳይሸጥ ቤተክርስቲያንን ወክየ አስተምራለሁ፡፡ በተዋልዶ ጤና ረገድም አራርቆና መጥኖ ባለመውለድ እናቶች በጤናቸው ላይ ጉዳት የሚደርስባቸው ከመሆኑም ባሻገር የሚወለዱት ህፃናት በተገቢው እንክብካቤ አለማደጋቸው ሌላው ችግር ነው፡፡ አምስት ደካማ ልጆች አከታትሎ ከመውለድ በማራራቅ ቦቾስ ቦቾስ ያሉ ቶሎ አድገው ቶሎ የሚላኩ፤ ቶሎ ለስነ-ምግባር የሚደርሱ ልጆችን መጥኖ መውለዱ ፋይዳው የጉላ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንዱን ስታጠባ ሌላውን ሣታሣድግ እንደገና በማርገዝ በወላጅና በልጆች ላይ ከሚደርሰው ጉስቁልና ባሻገር እናቶች በዚህ ሁኔታ በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ ባለቤታቸውን ማገዝ አለመቻላቸው እንዲሁ ሌላው ችግር ነው፡፡"

ሼህ ዳውድ እንድሪስ መሐመድ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ የተንታ ወረዳ የእስልምና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ናቸው። ተንታ ወረዳ በ02 ቀበሌ ከሚገኙ የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች ጋር በመሆን በቤተሰብ ምጣኔ፣ በጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና ኤች አይቪ ኤድስ ስርጭት መከላከል ረገድ በጋራ ይሰራሉ።



ሼህ ዳውድ እንድሪስ መሐመድ

"እኔና ቤተሰቦቼ የኤች አይቪ ኤድስ ምርመራ በማድረግ በቅድሚያ በአካባቢያችን ለሚኖሩ የማህበረሰቡ ክፍሎች አርአያ ሆነናል። ሌሎችም ተመርምረው ራሣቸውን እንዲያውቁ የምክር አገልግሎት እሰጣለሁ።

ከድህነት ለመላቀቅ በሚደረገው ጥረት የምንሰጣቸው ምክሮችና ትምህርቶች እጅግ በተጨባጭ ጠቃሚ በመሆናቸውና እኛም በዕምነቱ ተቀባይነት ስላለን ህብረተሰቡ በቀላሉ በመረዳት ተጠቃሚ ሆኗል።

ወንድ በሚስቱ፣ ሚስትም በባሏ አድረው ተፋቅረውና ሰላም ፈጥረው ተመክረው መኖር ተገቢ መሆኑን በመምከርና በማስተማር ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኤች አይቪ ቫይረስ ሥርጭት ዳንዳይኖሩ እሠራለሁ።"



“የአልማ ተዋልዶ ጤና ወኪሎች ለወረዳው የጤና እንቅስቃሴ ስኬት ወሣኝ ግብዓት ናቸው። ምክንያቱም በወረዳው የተገኘው ውጤት የተዋልዶ ጤና ወኪሎች፤ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የአመራር አካላት ተቀናጅተው በመስራታቸው ነው።

ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ውጤታማነት የአልማ ተዋልዶ ጤና ወኪሎች ሞዴሎቻችን ናቸው። ጤና ወኪሎቹ ለህብረተሰቡ ጤናም የመተላለፊያ ድልድዮች ናቸው። እነዚህ የአልማ ወኪሎች እምነታቸው የሞላ ነው። ምንም ነገር ሣይኖራቸው አምነውበት የተነሱበት በመሆኑ ክፍያ ሣይከፈላቸው ነው የወጡበትን ህብረተሰብ እያገለገሉ ያሉት።”

ሲስተር ጉዳድ ዓለሙ
የተንታ ወረዳ ጤና ጽ/ቤት ኃላፊ

አለምፀሐይ ዳውድ
በተንታ ወረዳ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ

"የአልማ የማኅበረሰብ አቀፍ የተዋልዶ ጤና ወኪሎች በሚያካሄዱት የቤት ለቤት ጉብኝት ለእናቶችና ህፃናት ጤንነት በመድረስ፤ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችንና ኤች.አይ.ቪ ኤድስን መከላከል እንዲሁም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት በመስጠት ረገድ ጠለቅ ብለው ገብተው እየሰሩ ነው፡፡

በዚህም ብቻ ሣይሆን የአልማ ተዋልዶ ጤና ወኪሎች አልማ በወረዳው ለሚያከናውናቸው ተግባራት ብቻ ሣይሆን፤ በወረዳው ጤና ለሚከናወኑ 16ቱ ፖኬጆች ስኬት መሰላል ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ የተዋልዶ ጤና ወኪሎችና የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አንድ ሆነን በመመካከር በመደጋገፍ በፕሮግራም መስራትም መለያችን ነው፡፡"

አልማ በፌስቱላ ላይ የከፈተው ዘመቻ ውጤታማ እየሆነ ነው

ይርከሙ አያል የሃያ አራት ዓመት ወጣትና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡ በአማራ ብሄራዊ ክልል፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን፣ ሸበል በረንታ ወረዳ፣ "ኮሸሽላ" በተባለች የገጠር መንደር (ጎጥ) ውስጥ ነዋሪ የሆነችዋ ወጣት ይርከሙ አያል በአንድ ወቅት የፊስቱላ ችግር አጋጥሟት ነበር፡፡

የዚህ መጽሄት ዝግጅት ክፍል ባልደረቦች ወደ መንደሯ ተጉዘን በደረስን ጊዜ በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ አልነበረችም፡፡ ዕለቱ ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም፣ ወቅቱም ትምህርት ቤት የሚዘጋበት ክረምት ቢሆንም፣ ከመንደሯ በትንሽ ኪሎ ሜትሮች ራቅ ብላ ወደምትገኘዋ ሞዠን ወደተሰኘች ትምህርት ቤት ለስብሰባ መሄዷ ከጎረቤቶቿ ተነገረን፡፡

እሷ ዘንድ ደርሰን ስናስጠራት መንግስት በነደፈው በአዲሱ የልማት ስትራቴጂ ላይ ለመወያየት ለስብሰባ መቀመጣቸውን ነገረችን፡፡ በማስከተልም፣ ከሰው ዓይን ሰውሮ በዝግ ጎጆ ውስጥ የሚሸሽግ የማያምር የፊስቱላ ችግር ትዝታዋንና በአገር የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ለሚያወያይ ስፊ አደባባይ ያበቃትን መፍትሄ እያነጻጸረች ልታጫውተን ፈቃደኛ ስለመሆኗ ጠየቅናት፡፡

ከዚያ በፊትም የፊስቱላ ሰለባ እንደነበረችና አማራ አቀፍ ልማት ማህበር በዘየደው መፍትሄ ለጤነኛነት መብቃቷን የሚያስረዳ ፖስተር ታትሞ መበተኑንና፣ አንዳንድ ሰዎች ጉዳዩን በተሳሳተ መንገድ ተረድተውት ይጠቋቆሙባት፣ የማግለል አዝማሚያ ያሳዩአት እንደነበር አስታወሰችን፡፡ በዚህም፣ በይፋ ለህዝብ ለሚበተን መጽሄት ቃሏን ባትሰጥ መልካም እንደሆነ፣ በተለይም መጽሄቱ በምትኖርበት አካባቢም የሚሰራጭ ከሆነ የአሉታዊ ተጽዕኖ ሸክሙ ከባድ እንደሚሆንባት ነገረችን፡፡

ይህ ሁኔታ የማግለልና የመድልኦ አስተሳሰብን የሚገታ ትምህርት ማስራጨት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር አንዱ ተግባር እንደሆነ ሁሉ፣ ፊስቱላን በመዋጋት ረገድም ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደሚገባ ሳይጠቁመን አላለፈም፡፡



ይህ በዚህ እንዳለ ሆኖ፣ ወጣት ይርከሙ አያልን ለማግባባት ያደረግነው ሙከራ ተሳክቶልን፣ “በፊስቱላ ላይ ተነሱ!” እያለ የሚጣራ ግለ ታሪኳን ተርካልናለች፡፡

ከዚህ በኋላ የሚነገረው ሙሉ ታሪክ የወጣት ይርከሙ አያል ነው፡፡ ተራኪዋም እሷ ነች፡፡ አተራረኳ ለጣልቃ ገብ ጥያቄ ብዙ ዕድል የሚሰጥ አልነበረምና፣ በወግ መካከል ስንቅር እየገባን የንግግር አንጓ እንድንሆን አላስቻለንም፡፡ አድምጧት!

የፊስቱላ መንስኤው ያለዕድሜ ጋብቻ ነው፡፡

እኔም ያለዕድሜዬ ነው ያገባሁት፡፡ ቤተሰቦቼ ሲድሩኝ ጋብቻ ምን እንደሆነ የማላውቅ ህጻን ልጅ ነበርኩ፡፡ “የማደጎ” ብለው ነው የሰጡኝ፡፡ በእኛ አገር አካሏ ያልጠናውንናምንምየማታውቀውን ህጻን ልጅ “አብራው እየኖረች ወዙን ለምዳ ትደግ” እያሉ ለወንድ ይሰጧታል፡፡ እኔንም፣ እንደዚህ “በማደጎ” ብለው፣ ለሦስት ዓመት ምንም ሳይነካኝ ልንቆይ ስምምነት አድርገው አጋቡኝ፡፡ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ላይደርስብኝ የተስማማው ባል ግን የሰጠውን ቃል ሻረ፡፡

ከዚህ በኋላ ያመኝ ጀመረ፡፡ በማደጎ የተሰጠሁትም ሆነ ቤተሰቦቹ ለእኔ ሊታመምኩት አላዘኑም፡፡ እንዲያውም፣ “ታማ አይደለም፣ ባልጋ ነው፣ ንቃህ ነው፣ ደህና አድርገህ በላት” አሉት፡፡ ከዚህ በኋላ ዱላ ቀለቤ ሆነ፡፡ በየቀኑ ይደበድበኛል፡፡ ጩኸቴ ጎረቤቱን ሁሉ የሚረብሽ ችግር ሆነባቸው፡፡ አብዝቶ የሚያስጮኸኝ ዱላው አይደለም፡፡ ዱላው ምንም አልመሰለኝም፡፡ የማልችለው ስቃይ የሆነብኝ ህመሙ ነው፡፡

እየተወዘወዝኩኝ ማልቀስና መጮኼን የማልተው ስሆንባቸው ወደቤተሰቦቼ መልዕክት ላኩ፡፡ “ኑና ምከሯት፣ ረበሸች” ብለው ነው መልዕክት የላኩባቸው፡፡ እንደተባሉት፣ ቤተሰቦቼ መጥተው ለምን እንደምረብሽ ጠየቁኝ፡፡ ለሦስት ዓመት ላይደርስብኝ፣ ላይነካኝ የገባውን ቃል እንዳላከበረ ነገርኳቸው፡፡ ቤተሰቦቼ አላመኑኝም፡፡ “ከእሱ ጋር አልተኛም ብላ አስቸግራ ነው” በማለት የነገሯቸውን የወንዱን ቤተሰቦች ግን አመኗቸው፡፡ ቤተሰቦቼ ከእሱ ቤተሰቦች ጋር ሽርክና ፈጥረው መፍትሄ ሳይሰጡኝ ተመልሰው ሄዱ፡፡

ሕመሜ እየባሰ ሄደ፡፡ የገጠር ሙሽራ ከጫጉላ አይወጣም፡፡ ሳይታወቅ የምወጣበት ትንሽ አጋጣሚና ቀዳዳ አጣሁ፡፡ የመውጣት ዕድል ቢኖረኝ፣ ራሴን ማጥፋት ነበር የምፈልገው፡፡ እህልም አልበላኝ አለ፡፡ ውሃ ብቻ እየጠጣሁ አርባ ቀን በጫጉላ ውስጥ ቆየን፡፡ ይህን ያህል ጊዜ ሁሉ፣ የወንዱ ቤተሰቦች ህመሜን አያውቁልኝም፡፡ ክፋተኛ ነበረ የሚያደርጉኝ፡፡

ከአርባ ቀን በኋላ ግን ቤተሰቦቼ፣ ወንድሞቼና እህቶቼ መጡ፡፡ የመጡት ከጫጉላ ወጥተን ከአማቶቼ ጋር ለመቀላቀል ነው፡፡ “መግለጫ” ይባላል፡፡ በባህላችን እናትና አባት ለመግለጫ አይመጡም፡፡

ወንድምና እህቶቼ መጥተው ተቀላቀልን፣ በዚያው ዕለት “ወደ ቤተሰቦቼ ካልሄድኩኝ ሞቼ እገኛለሁ” አልኩኝ፡፡ ከአማቶች ጋር ተቀላቅለህ በዕለቱ ወደ ቤተሰብ አይኬድም፣ ነውር ነው፡፡ በዚህም ጎረቤቱ በሙሉ ሰደበኝ፡፡ “ስትመጣም ረባሽ፣ አሁንም ረባሽ” እያሉ በቁጣ ተናገሩ፡፡ የትልቁ ትልቅ ወንድሜ ግን “ትምጣ” ብሎ ሃሳቤን ደገፈልኝ፡፡ ከዚህ በኋላ “አትሄድም” ብለው ከእሱም ጋር ተጣሉ፤ እስከመሰዳደብም ደረሱ፡፡

ወንድሜ ሃሳቡን ባለመለወጡ ወደ ቤተሰቦቼ ይዘውኝ ሄዱ፡፡ መሄዴን ያልወደደው አባቴ “ለምን መጣሽ?” ብሎ ደበደበኝ፡፡ በራሳቸው ፈቃድ እንዳመጡኝና እንዲተወኝ ወንድሞቼ ሲነግሩት ለግዜው ተወኝ፡፡

ቤተሰቦቼ ዘንድ ተመልሼም እረፍት የለኝም፡፡ የቤት ውስጥ ብዙ ሥራ እሰራለሁ፡፡ ሕመሜም ከአደር አደር እየበረታ እንጅ እየተሻለኝ የሚሄድ አልሆን አለ፡፡ “ሕመሜ በወንድ የመጣ ነው”ስለምል፣ “ከወንድ በመራቄ ይሻለኛል” የሚል ሃሳብ ነበረኝ፡፡ እንዳሰብኩት፣ ከወንድ መራቄ አላሻለኝም፡፡ ስቃዬ እየበዛ፣ ሰገራ መቆጣጠር እያቃተኝ ሄደ፡፡ አስተካክየ መራመድም አቃተኝ፡፡ ፈርከክ እያልኩኝ የምሄድ ሆንኩኝ፡፡

ቤት ውስጥ አብራኝ ስለምትውል፣ ይህን ችግሬን የምታውቀው እናቴ ብቻ ናት። ውጪ ስለሚውሉ፣ ወንዶቹ አያውቁትም። ማታ ሲመጡም እነሱ ፊት አልቀርብም። ወደ ውስጥ፣ ወደ አልጋ ቤት እገባለሁ። ወይም ወደ ማድቤት ሄጄ ሥራ እይዛለሁ። ከእናቴ በቀር አባቴና ወንድሞቼ ሳያውቁት፣ እንደዚህ እየተሰቃየሁ ስድስት ዓመት አሳለፍኩኝ።

በሽታው መጥፎ ጠረን ያመጣል። ቤተሰቦቼ ሀብታም አይደሉም፣ ድሃ ናቸው። እናቴ ግን፣ እንደምንም ብላ፣ ልብስ ትገዛልኛለች። ቶሎ ቶሎ እየታጠበ እቀያይራለሁ። ቤታችንን ሁልጊዜ ሰንደል ታጨስበታለች። በአንድ ግዜ ብዙ ሰንደል ነው የምታጨሰው። በዚህ መንገድ ጠረኑ በሌሎች ሳይታወቅ ለብዙ ግዜ እንዲቆይ ማድረግ ችላለች።

ከስድስት ዓመት በኂላ፣ አባቴ "ጓደኞቿ ትዳር ይዘው እሷ እዚህ ምን ታደርጋለች? ወይ ታግባ፣ ወይ ከዚህ ቤት ትውጣ!" ማለት ጀመረ። በዚህ ምክንያት ከእናቴ ጋር በጣም ተጣሉ። እኔም "አላገባም" አልኩኝ። አባቴ በራሱ ከሌሎች ጋር በጎን ተነጋግሮ ጨርሶ ሊያጋባኝ ጨርሶ ነበር። ለእነዚያ ሰዎች ዝም ብለው መጥተው እንዲጠይቁ ነገራቸው። እነሱም ሽማግሌና ቄስ ይዘው መጡ። ብቻቸውን፣ እርስ በርሳቸው ተነጋግረው ይዘውኝ ሄዱ፤ ለሌላ ባል ተሰጠሁ።

ሳልፈልግ ካጋቡኝ ሁለተኛ ባል ሄጄ ከእሱ ጋር ለመገናኘት ፈቃደኛ አልሆንኩም። እሱም፣ "ቀስ ብየ እደርስበታለሁ" በሚል ነው መሰለኝ፣ አላስገደደኝም። የተሸከምኩትን የህመም ችግር ግን አያውቅም። ስላልቸኮለና ስላላስገደደኝ አመሰግነዋለሁ፤ ለእሱ ትልቅ ከበሬታ ነው ያለኝ። ምንም ሳይደርስብኝ፣ ከእነሱ ቤት ሁለት ቀን ብቻ አድሬ፣ በሦስተኛው ቀን "ሹልክ" ብዬ ጠፍቼ ሄድኩባቸው። ወደ ቤተሰቦቼ ስመለስ፣ ጠፍቼ መምጣቴን ያላወቀው አባቴ ብቻ ነው። አጠገባችን ቤት ሠርቶ የሚኖር ወንድም አለኝ። በዚህ ወንድሜ ቤት ውስጥ አንድ ወር ስቀመጥ አባቴ አያውቅም።

ወንድሜ ቤት ውስጥ መዋሌን ስላልወደደው፣ ትምህርት ቤት ብገባ መልካም እንደሆነ አነሳልኝ። እኔም ተስማማሁና ተመዝግቤ የ3ኛ ክፍል ትምህርቴን መከታተል ጀመርኩኝ። በአጋጣሚ የሚያስተምሩኝ መምህራን ጎረቤቶቻችን ነበሩ። በልብስ ማጠብም፣ በሌላም ስራ ስለማግዛቸው በጣም ይወዱኛል። ደብተርና እስክርቢቶ ይገዙልኛል። ለትምህርቴ እንቅፋት የሆነብኝ ህመሜ ብቻ ነበር። ተማሪዎች መማሪያ ክፍል ውስጥ ከእኔ ጎን አይቀመጡም። በተለይም የ6ኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ ነበር ተማሪዎች አብዝተው የሚሸሹኝ። በዚህ ጊዜ ህመሜ በጣም ጠንቶ ከልክ በላይ ያሰቃየኝ ነበር። ተማሪዎቹ ግን ከእኔ የሚያሸሻቸውን ምክንያት አያውቁትም። የውስጤ ስቃይ ሳያንሰኝ፣ የተማሪዎቹ ሽሽት ሌላ የጭንቀት ስቃይ ጨመረብኝ። "እንዲህ ብዬ ልንኖር ነው ወይ?" እያልኩኝ ማሰላሰል ጀመርኩኝ። በጣም መረረኝ። ራሴን ለመግደል ወሰንኩኝ። ቤታችን ውስጥ የነበረን የአይጥ መርዝ ዱቄት በውሃ በጥብጬ ጠጣሁት። ነገር ግን አላደለኝም፣ መርዙ ጊዜው ያለፈበት ነበረና ሳይገድለኝ ቀረ።

አባቴ "አጋባኒት" ብሎ ካላከኝ ሁለተኛ ባል ጠፍቼ መምጣቴን ያወቀው ዘግይቶ ነው። መመለሴን ያወቀ ዕለት ተናደደ። ለቤተ ዘመድ በሙሉ ሮሮ ማሰማት ጀመረ። "ለምንድን ነው ራሷን የማትችል? እዚህ ሆና ገንዘቤን ልትጨርስ ነው ወይ?" እያለ ለሁሉም ተናገረ። እኔን "ከንቱ ናት" እያለ ለሚያወራብኝ ወሬ ማሳመኛ እንዲሆነው፣ ባል አግብታ እዚያው "ልጥፍ" ብላ የቀረችውን ትንሽ እህቴን ምሳሌ እያደረገ አነሳት።
ከዚያ ወዲህ፣ ወንድሞቹ የእርሻ መሬት ተከራይተው ያዙልኝ። "ይህን ይዘሽ ራስሽን አስተዳድሪ" አሉኝ። ራሳቸው እያረሱልኝ፣ ጤፍ እየዘራሁ ሳንቲም መያዝ ጀመርኩኝ። ከ6ኛ ወደ 7ኛ ክፍል ስዛወር፣ ክረምት ላይ ወደ ህክምና ለመሄድ አሰብኩ። በዚህ ጊዜ እህል ሼጬ ብር 2,200 (ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ብር) ነበረኝ። ግን፣ ሩቅ ቦታ ወዳለ ህክምና የሚወስድ ህመም እንዳለብኝ እንዴት ብዬ ልናገር?

እናቴ ዓይኗን ያማታል። እሷ አይኗን እንደምትታከምና እኔ ይዣት እንደምሄድ አስመስላ ለአባቴ ነገረችው። በዚህ ተስማምተው፣ እኔና እናቴ ተያይዘን ወደ ደብረ ማርቆስ ከተማ ሄድን። የደብረ ማርቆስ ከተማ ሃኪሞች የእኔን ህመም ማከም እንደማይችሉ ነገሩኝ። ወረቀት ጽፈው ሰጡኝና ወደ አዲስ አበባ ላኩኝ። አዲስ አበባ የሄድኩበትን ሆስፒታል ስሙን አላስታውሰውም። እነሱም ዘንድ አንዲት ሃኪም "ሦስትና አራት ሺህ ብር ከሌለሽ መዳን አትችይም" አለችኝ። "የለኝም" ብዬ፣ ከእናቴ ጋር ተመልሰን ወደ ቤታችን መጣን።

ከአዲስ አበባ መልስ፣ የተረፈችኝን ገንዘብ ይዤ፣ "የዱሃ" ወደምትባለው የወረዳችን ከተማ ሄድኩኝና በወር ሃምሳ ብር የሚከፈልበት ቤት ተከራይቼ ብቻዬን መኖር ጀመርኩ። ህመሜ እንዳይታወቅ ስል፣ የኪራዩን ወጪ የሚካፈለኝና አብሮኝ የሚኖር ደባል ጓደኛ አልፈለግኩም።

የዱሃ ከተማ ከተከራየሁበት ቤት ጎረቤቴ ሆና የምትኖር አንዲት ሴት ነበረች። የሴቶችን ጉዳይ የምትከታተልና በየገጠሩ እየሄደች የምታስተምር ናት። ፍርኖዬ ትባላለች። አንድ ቀን ቤቷ ውስጥ ቡና አፍልታ ጠራችኝ። ከእሷ ጋርም ከሸበል ወረዳ ያመጣቻት ሌላ ልጅ ነበረች። ያቺን የሸበል ልጅ ሳያት፣ አቀማመጧ ዘና ያለ አይደለም። በዚህም፣ የእኔን የመሰለ

ችግር እንዳለባት ጠረጠርኩኝ፡፡ ልጅቱ ምን ሆና እንደሆነ እንድትነግረኝ ፍርናዬን ጠየቅኋት፡፡

"በህጻንነቷ ወልዳ የሽንት ፊኛዋና ማህጸኗ ለብልሽት ተዳርጎ ነው፡፡ ሽንቷን መቆጣጠር አትችልም፡፡ ለህክምና ወደ ባህር ዳር ልወስዳት ነው " አለችኝ፡፡

"እኛ አገርም እንደዚህ ያለ ችግር ያለባት አንዷት ልጅ አለች፡፡ ታድኛታለሽ ወይ?" አልኳት፡፡

"አዎ! አድናታለሁ፡፡ በነፃ ነው የማሳክማት፡፡ ስሟን ንገሪኝና ላግኛት" አለችኝ፡፡
"ስሟን ጠይቄ ልምጣ" ብያት ተለያየንና፣ ጉዳዩን ለእናቴ ነገርኳት፡፡ እናቴ በሁኔታው ተስማማች፡፡

ወደ ፍርናዬ ተመልሼ ችግሩ የራሴ መሆኑን ነገርኳት፡፡ አላመነችኝም፡፡ ጎረቤት ሆነን ለብዙ ጊዜ አብረን ስንኖር፣ ለሷም ሆነ ለሌሎቹ የህመሜ ጠረን ገጥሟቸው አያውቅም፡፡ እኔም ብዙም አልቀርባቸውም ነበር፡፡ ቤቴ ውስጥ ሆኜ፣ በሬን ገርበብ አድርጌ መቀመጥ አዘወትራለሁ፡፡ ትምህርቴን እያጠናሁ ይመስላቸዋል፡፡

ፍርናዬ እዚያው የዱሃ ወደሚገኝ ሃኪም ቤት ወሰደችኝ፡፡ ስታስመረምረኝ፣ ዶክተር ስማቸው የሚባል ሃኪም የፊስቱላ ችግር እንዳለብኝ ነገራት፡፡ ከዚህ በኋላ ሳምንት አልቆየችም፡፡ "ነገ ወደ ባህር ዳር እንሄዳለን፣ ይህንም ለቤተሰቦችሽ ንገሪያቸው" አለችኝ፡፡ ለአባቴና ለወንድሞቼ ጭምር፣ ለሁሉም ቤተሰቦቼ ነገርኳቸው፡፡ እነሱም አላመኑኝም፡፡ "ደካማ (ነፍሰ ጡር) ሆና ነው" አሉኝ፡፡
ከባህር ዳር መኪና መጣ፡፡ መኪናውን የላከው አልማ መሆኑን ያወቅሁት ዘግይቼ ነው፡፡ ከየዱሃ ከተማ ወደ ባህር ዳር ለመሄድ መንደራችንን ስለምናቋርጥ፣ ከማለዳው ሁለት ሰዓት ወደ መንገድ ዳር ወጥተው እንዲጠብቁኝ ለቤተሰቦቼ ነግሬያቸው ነበር፡፡ ሹፌሩ ግን መንገድ ስቶ ወደ ሸበል ሄዶ ስለነበር፣ ተመልሶ የዱሃ የደረሰው አራት ሰዓት ሲሆን ነው፡፡ የዘገየሁባቸው ቤተሰቦቼ ግን የቀረሁ ወይም ተሻልኬ የሄድኩ አድርገው ቆጠሩት፡፡ "ደካማ ነች" ያሉኝንም እውነት አስመሰለላቸው፡፡

ባህር ዳር ሄጄ ለሦስት ሳምንት ሆስፒታል ውስጥ ተኛሁ፡፡ በሦስት ሳምንት ድኜ መጣሁ፡፡ በተመሳሳይ የፊስቱላ ችግር አልማ ወደ ባህር ዳር አንድ ላይ ወስዶ ያሳከመን ከእኔ ጋር ሦስት ነን፡፡ እነሱም ድነው ተመለሱ፡፡

አሁን ጤንነቴ በጣም የተሟላ ነው፡፡ "በአመትሽ እንድትመጪ" ተብዬ ወረቀት ሰጥተውኝ አምና ሄጄ ነበር፡፡ "ድነሻል" ብለው ሸኙኝ፡፡ ድኜ ስመለስ፣ ለመጓጓዣ እንዲሆነኝ፣ አልማ 150 ብር ሰጠኝ፡፡ ለአባቴ ብርድ ልብስ ገዛሁ፡፡ ቤቴ ዘንድ ስደርስ የጎረቤት ልጆችን በሙሉ ጠርቼ ግብዣ አደረኩላቸው፡፡ የደስታዬ ተካፋይ አደረግኳቸው፡፡

አባቴ" ለምን ሳትነግሪኝ ቀረሽ?" እያለ ወቀሳ ነገር አቀረበብኝ፡፡ "እኔ አስፈራለሁ ወይ?" አለኝ፡፡ ከዚያ ወዲህ ይወደኛል፡፡ ከዓይኑ ስሰወር እንኳን አያምነኝም፡፡ ወንድሞቼም በጣም ይወዱኛል፡፡ ይንከባከቡኛል፡፡ "ሰዎች ፀንሳ ነው እያሉ ይነግሩን ስለነበር ጠልተንሽ ነበር" አሉኝ፡፡ አሁን ሁሉም መልካም ነው፡፡ አልማ ለዚህ ስላበቃኝ አመሰግናለሁ፡፡ ፍርናዬንም አመሰግናታለሁ፡፡ እናንተም አመስግኑልኝ፡፡

በአልማ የተደራጁ ወጣት ሴቶች ፊስቱላን ሲዋጉ

ምሥራቅ ጎጃም ዞን ሸበል በረንታ ወረዳ

አቢሲንያና አደይ አበባ በምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ ሸበል በረንታ ወረዳ፣ የዱሃ ከተማ የሚገኙ በአማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) የተደራጁ የሴት ወጣቶች ክበባት ናቸው። የሁለቱም ክበባት ዓላማ ፊስቱላን መዋጋት ነው።

ከእነዚህ ሁለት ክበባት የተውጣጡ ስድስት ወጣቶች ጋር የአልማን ‹‹ፊስቱላን እንዋጋ›› ፕሮጀክት ለማስፈፀም በወረዳቸው በሚያከናውኗቸው ተግባሮች ላይ ያተኮረ አጠር ያለ ውይይት አድርገናል።

ከአቢሲኒያ የሴት ወጣቶች ክበብ አባላት

በአልማ የተደራጁ ወጣት ሴቶች ፌስቱላን ሲዋጉ

ምሥራቅ ጎጃም ዞን ሸበል በረንታ ወረዳ

አቢሲንያና አደይ አበባ በምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ ሸበል በረንታ ወረዳ፣ የዱሃ ከተማ የሚገኙ በአማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) የተደራጁ የሴት ወጣቶች ክበባት ናቸው። የሁለቱም ክበባት ዓላማ ፊስቱላን መዋጋት ነው።

ከእነዚህ ሁለት ክበባት የተውጣጡ ስድስት ወጣቶች ጋር የአልማን ‹‹ፊስቱላን እንዋጋ›› ፕሮጀክት ለማስፈፀም በወረዳቸው በሚያከናውኗቸው ተግባሮች ላይ ያተኮረ አጠር ያለ ውይይት አድርገናል።

ከአቢሲኒያ የሴት ወጣቶች ክበብ አባላት

የግፍ አሸነፍ

ጥያቄ፡- በአማራ ብሔራዊ ክልል የፌስቱላ ችግር ጎላ ብሎ ከሚታይባቸው አካባቢዎች አንዱ የእናንተ ወረዳ የሆነው ለምንድን ነው?

የግፍ አሸነፍ፡- መነሻው ያላቻ ጋብቻ ሲሆን፣ በተለይም በወሊድ ጊዜ ለጋ በመሆናቸው ምክንያት ማህፀናቸው ይጎዳል፡፡ ምጥ ሲይዛቸው ወደ ጤና ጣቢያ አያመጧቸውም፡፡ ሆዳቸውን በቅቤ እያሹ ሊያዋልዷቸው ይሞክራሉ፡፡

ከወሊድ በፊትም ቢሆን፣ ለአካለ መጠን ያልደረሱ በመሆናቸው ምክንያት፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አማካኝነት ለበሽታው የሚዳረጉ አሉ፡፡

የአማራን ክልል በልማት ኢትዮጵያን እናለማለን!

ማንአህሎሽ ብዙአዬ

ማንአህሎሽ ብዙአዬ፡- እዚህ አካባቢ ህፃናት ሴቶች ከስምንት ዓመታቸው ጀምሮ እንዲያገቡ ይደረጋሉ፡፡ ከ8 እስከ 9 ዓመት ያለችን ህፃን ለባል የሚሰጧት ‹‹የማደጎ›› ብለው ነው፡፡ ከዚያ በላይ ከ11 እስከ 18 ዓመት የሆነች ደግሞ በቀጥታ ለጋብቻ እንደደረሰች ትቆጠራለች፡፡

‹‹ሴት ልጅ ሹራብ ነች›› የሚሉት አባባልም አለ፡፡ ‹‹ሹራብ ይለጠጣል፣ አይቀደድም፤ ሴት ልጅም እንደዚያው ነች ትችላለች›› ማለታቸው ነው፡፡

ቀድማ የወር አበባ ካየችም ‹‹ልጅ ከወንድ ጋር ተገናኝታለች፣ ክብረ ንፅህናዋ የለም›› ብለው ስለሚያምኑ ቶሎ ይድሯታል፡፡ ‹‹ሴት ልጅ ደረቷ ላይ ጡት ከታዬ መዳር አለባት›› ባይ ናቸው፡፡

እነማይ መኮንን

ጥያቄ፡- ይህን ችግር ለማስወገድ ምን ምን ተግባሮችን ታከናውናላችሁ?

እነማይ መኮንን፡- አንዱ ተግባራችን ማስተማር ነው፡፡ ለፌስቱላ መነሻ የሆኑትን ችግሮች በሙሉ እያነሳን፣ ድርጊቱ ጎጂ ልማድ መሆኑንም እየነገርን በየገጠሩ ቀበሌዎች በመዞር እናስተምራለን፡፡

ሴት ልጅ መቼ ጡት እንደምታወጣ፣ የወር አበባ መቼ እንደምታይ፣ ለጋብቻ የምትደርሰው መቼ እንደሆነ እናስረዳለን፡፡ የምናስተምርበት የቡና ጠጡ ፕሮግራምም አለን፡፡

ሁለተኛው ተግባራችን ደግሞ የፌስቱላ ችግር ያለባቸውንና ተደብቀው የተቀመጡ ሴቶችን አፈላልገን ወደ ህክምና መላክ ነው፡፡

በነገራችን ላይ፣ የፌስቱላ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ገለል አድርገውና ኩሽና መሳይ ሰርተው ለብቻቸው ነው የሚያስቀምጧቸው፡፡ የሚያገሏቸው፣ በሽታው ጠረን የሚያመጣ ስለሆነ፣ ከጠረኑ ለመራቅ ነው፡፡ በዚያ ላይ ፌስቱላን ‹‹የሰይጣን ልክፍት ነው›› ይሉታል፡፡ በዚህም ምክንያት ‹‹በህክምና አይድንም›› ይላሉ፡፡ ይህን ሁሉ አልፈን ነው የታመሙትን አፈላልገንና አግኝተን ወደ ህክምና የምንልካቸው፡፡

ማማር መኮንን

ጥያቄ፡- ይህ ጎጂ አስተሳሰብና ድርጊት ከሕብረተሰቡ ጋር ለረዥም ጊዜ የቆዩ ነውና፣ የምትሰጡትን ትምህርት በቀላሉ ያለመቀበል፣ ህመምተኛ መኖሩን ለማሳወቅም ሆነ ወደ ህክምና ለመላክ ፈቃደኛ ያለመሆን ችግር አያጋጥማችሁም?

ማማር መኮንን፡- የዚህ ዓይነት ፈታኝ ችግር ያጋጥመናል፡፡ ቢሆንም፣ ለማሳመን ጥረት ከማድረግ አንቆጠብም፡፡ የምንሰጣቸውን ትምህርት በፍጥነት ተቀብለው በተግባር የሚያውሉም አሉ፡፡ እነዚህ በማስተማር ላይ እያለን ‹‹የእገሌ ልጅ፣ እገሌ የምትባል አለች›› የሚል ጥቆማ እዚያው ይነግሩናል፡፡ ባገኘነው ጥቆማ መሠረትም ህመምተኛዋ ልጅ ወዳለችበት ቦታ እንሄዳለን፡፡

አንዳንዶች ‹‹ልጃችንን አንሰጥም፣ በህክምና አይድንም›› ይሉናል፡፡ በህክምና እንደሚድንና ህክምናው በነፃ እንደሚሰጥ፣ ወጪ እንደማያወጡ በተደጋጋሚ እናስረዳቸዋለን፡፡ ፈቃደኛ ይሆናሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ህመምተኛዋን የወለደች ከሆነች ከልጇና ከቤተሰቧ ጋር፣ ከባሏ ጋር ከሆነችም ከእሱ ጋር ሆነው ወደ ወረዳው ጤና ጣቢያ እንዲመጡ እናደርጋለን፡፡ መጀመሪያ በሽታው ፊስቱላ መሆኑ መረጋገጥ ስላለበት ነው በወረዳ ጤና ጣቢያ ምርመራ የሚደረገው፡፡ መሆኑ ሲረጋገጥ እንዲታከሙ ባሕር ዳር ፊስቱላ ሆስፒታል ድረስ ወስደን እናስረክባለን፡፡

ጥሩሰው ካሴ

ጥያቄ፡- በፊስቱላ ላይ ዘመቻ ለማድረግ የሚያስችላችሁን ግንዛቤ ያገኛችሁት ከየት ነው?

ጥሩሰው ካሴ፡- ክበቦቻችን እንዲመሰረቱ ያደረገው አልማ ነው፡፡ መጀመሪያ አልማ ስልጠና ሰጥቶናል፡፡ ስልጠናውን የወሰድነው ደብረ ዘይት ሄደን ለሰባት ቀን ነበር፡፡ በፊስቱላ ላይ ያተኮረ ስልጠና ነው፡፡ ከዚያ ስንመለስ ሥራ ጀመርን፡፡

በሌላ ጊዜም ከሁለቱ ክበቦች 9 አባላት ተመልምለው በአልማ የአቻ ለአቻ መማር ስልጠና ወስደዋል፡፡ የአቻ ለአቻ መማር ፆታን አይለይም፡፡ ወንድንም ሴትንም ያካትታል፡፡ ለምሳሌ፣ 18 ዓመት የሞላት ሴት ከሌላ የእድሜ አቻዋ ወንድ ጋር ሆነው ስለ ተዋልዶ ጤና ምንነት እንዲያውቁ እናስተምራለን፡፡ ሴቷ ለአቅመ ሄዋን ስትደርስ አቻዋ ከሆነና ለአቅመ አዳም ከደረሰ ወንድ ጋር በፍላጎቷ መጋባት እንዳለባት፤ ከፍላጎቷ ውጪ የሚመጣባትን ጥያቄና ተፅእኖ በሙሉ መቋቋም እንዳለባት እናስረዳለን፡፡

በአቻ ለአቻ መማር ስልጥነን እኛም የምናስተምረው ያለዕድሜ ጋብቻን የሚያስቀርና ለፊስቱላ መንስኤ የሆነውን ይህን ችግር ስለሚያስወግድ ነው፡፡

ሽምበራ አድማሱ

ጥያቄ፡- እስካሁን በሠራችሁት ሥራ የተገኘውን መልካም ውጤት በምን ትመዝኑታላችሁ?

ሽምበራ አድማሱ፡- በእኛ ክበብ በኩል ስናስተምር ጥቆማ እየተሰጠን 4 ሴቶችን አግኝተን ወደ ህክምና ልከናል። ሁሉም ድነው መመለሳቸው ያረካናል።

ትልቁ ቁም ነገር ግን በማስተማራችን ሕብረተሰቡ ውስጥ የተፈጠረው የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። በበተንነው በራሪ ወረቀት ሳይቀር ግንዛቤ ይዞ ‹‹ባለቤቴ የዚህ ህመም ተጠቂ ናት›› ብሎ ያመጣ ሰው አለ። በእርግጥ፣ ስትመረመር ህማሟ ፊስቱላ አልነበረም። የአስተሳሰብ ለውጡ ግን ያስደስታል።

ከድህነት ጋር ተሳምደን አንኖርም!

ጥያቄ፡- አልማ ካደራጃችሁና ስልጠና ከሰጣችሁ በኋላ ለመነሻም ሆነ በተከታታይ ለሥራችሁ የሚያስፈልጓችሁን ነገሮችና ድጋፎች የምታገኙት ከየት ነው?

የግፍ አሸነፍ፡- ዋነኛው ደጋፊያችን አልማ ነው፡፡ ከደብረ ዘይት ስልጠና ስንመለስ አልማ የቢሮ እቃዎችንና ሌሎችንም አሟልቶልናል፡፡ አልማና አስተዳደሩ ተወያይተው በደረሱበት ስምምነት መሠረት አስተዳደሩም ቢሮ ሰጥቶናል፡፡

ለእያንዳንዱ ተግባራችን አልማ የመደበልን በጀትም አለን፡፡ የፊስቱላ ህመምተኞችን ማፈላለግ፣ የቡና ጠጡ ፕሮግራም፣ የአቻ ለአቻ መማማር ለየራሳቸው የተመደበላቸው በጀት አላቸው፡፡ ቢሮአችን ዝግ እንዳይሆን ማበረታቻና መንቀሳቀሻም ይሰጠናል፡፡ ህመምተኞችን ይዘን ባሕር ዳር ፊስቱላ ሆስፒታል ስንወስድም የትራንስፖርትና አበል ወጪያችንን የሚሸፍነው አልማ ነው፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ የወረዳው አስተዳደር፣ ሴቶች ጉዳይ፣ የጤናና የወጣቶች ባህልና ስፖርት ጽ/ቤቶች በሥራችን የሚተባበሩን ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ናቸው፡፡

ከአደይ አበባ የሴት ወጣቶች ክበብ አባላት

አልማን ሲደግፉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ይዋጋሉ፤
የጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች ሰለባዎችን ይታደጋሉ።

አልማን ይደግፉ!

አማራ አቀፍ ልማት ማኅበር (አልማ)

Amhara Development Association (ADA)

አድራሻ: በህርዳር ስልክ: 058 220 0983 ፋክስ: 058 220 1088 ፖ.ሳ.ቁ. 307 e:mail ada.hq@ethionet.et
አዲስ አበባ ስልክ: 011 551 7886 ፋክስ: 011 551 7795 ፖ.ሳ.ቁ. 13685 e:mail ada.liaison@ethionet.et
www.amharada.org

ፍርኖዬ ዳኜ - ያልተዘመረላት ፀረ-ፌስቱላ ታጋይ

ወጣት ፍርኖዬ ዳኜ ቀደም ሲል በሸበል በረንታ ወረዳ ‹‹ሞዦን›› የተባለች የገጠር ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ ነበረች፡፡ አሁን ግን ነዋሪነቷ ‹‹የዱሃ›› በተሰኜችዋ የወረዳው ዋና ከተማ ሲሆን፣ የአማራ ሴቶች ማህበር የሸበል በረንታ ወረዳ ጽ/ቤት ቅጥር ሠራተኛ ነች፡፡ ወጣት ፍርኖዬ ዳኜ የማንኛውም የፀረ ፊስቱላ ክበብ አባል አይደለችም፡፡ በፊስቱላ ላይ በእልህ የተነሳች ስለመሆኗ ግን በብዙዎች ይመሰክርላታል፡፡ በየዱሃ ከተማ ቆይታችን እሷንም አነጋግረናታል፡፡

ፍርኖዬ ዳኜ

ፍርኖዬ ዳኜ ለመነሻ የሚሆናትን ስለ ፊስቱላ መጠነኛ መረጃና ግንዛቤ ያገኘችበትን አጋጣሚ እንዲህ ትገልፃለች፡-

‹‹የአማራ ሴቶች ማህበር ዓመታዊ ግምገማ ለሚደረግበት ስብሰባ በ1999 ዓ.ም ወደ ደብረ ማርቆስ ከተማ ተጠርተን ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ የፊስቱላ ጉዳይ በማሳሰቢያ መልክ ቀረበ፡፡ ስለመንስኤውና ህመሙ፣ ስለሚታወቅበት ምልክቱ ተነገረን፡፡ ህመምተኞችን ስናገኝ ወደ ህክምና እንድንወስድና ህክምናውም በነፃ እንደሚሰጥ ተገለፀልን፡፡

‹‹ወደ ወረዳዬ ስመለስ በየገጠሩ ቀበሌዎች ለማስተማር ተሰማራሁ፡፡ ሴቶች ያለቀስቃሽ ወጥተው በልማት እንዲሳተፉ፣ ለመብታቸው ራሳቸው እንዲቆሙ፣ የሥራ ብቻ ሳይሆን የንብረት ባለቤትነት ተሳታፊም እንዲሆኑ አስተምራለሁ፡፡ ከዚህ ጋር ሁለተኛው የማስተማር ርዕስ የፊስቱላ ጉዳይ እንዲሆን አደረግሁ፡፡››

አፈላልጌ እያገኘኋቸው ወደ
አልማ የላክኋቸውና
አሳክሚቸው የተመለሱት
በጠቅላላ 17 ናቸው።
ሁሉም ድነውልኛል።
ሳገኛቸው ሮጠው መጥተው
ይስሙኛል። ለእኔም ሆነ ለአልማ
ያላቸው ፍቅር የተለየ ነው።

ፍርኖዬም የፌስቱላ መንስኤው ያለ ዕድሜ ጋብቻ መሆኑን ትገልፃለች፡፡ ‹‹የአካባቢውን ሕብረተሰብ ያላቻ ጋብቻን ከመልካም ነገር እንዲቆጥር የሚያደርጉት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ስንል ጠየቅናትም፡፡

‹‹ያለ ዕድሜ ጋብቻ የሚፈፀመው ‹‹የእገሌ ልጅ ሳታመልጠኝ፣ ሳያመልጠኝ›› እየተባለ ዝምድና በመፈለግ ነው፡፡

‹‹በአካባቢያችን ባል ሚስቱን ክፉኛ ይደበድባል፡፡ በተለይ ሚስቱ በተከታታይ ሴት ከወለደች ሁልጊዜ የራሷን የቤት ሠራተኛ ነው የምትወልደው› እያለ በጥላቻ ዓይን ይመለከታታል፡፡ ሌላ ወንድ የወለደች ሴት ካለች ይመኛታል፡፡ ያልወለደች ብትሆንም ‹‹ወንድ ልትወልድ ትችላለች›› በሚል ቀልቡን እሷ ላይ ያሳርፍና በሚስቱ ላይ ፊቱን ያዞራል፡፡ ብዙ ስቃይም ያደርስባታል፡፡

‹‹ከዚህ ስቃይዋ በተነሳ ሚስት የወለደቻትን ሴት ልጅ ያለ ዕድሜዋ ድራ ልትሸኛት ትገፋፋለች፡፡ ሴት በወለደች ሚስቱና ሴት ሆና በተወለደች ልጁ ላይ ትልቅ ጥላቻ ከሚያሳድር ባል ጋር ለመኖር ያዳግታታል፡፡ የመፋታት አደጋ እንዳለ ስለሚሰማት ከባሏ ከመለያየቷ በፊትና መዳሪያ ድግስ ሳይጠፋ ህፃን ልጇን አጋብታ መገላገልን ትመርጣለች፡፡

‹‹በሌላ በኩልም፣ ‹እናቴ ሳትሞት፣ አያቴ ሳትሞት ልጄን በእነሱ አስመርቄ መዳር አለብኝ› እያሉ ሴት ልጆቻቸውን ያለዕድሜያቸው የሚያጋቡ ብዙ ናቸው፡፡››

በመጨረሻም፣ ወጣት ፊርኖዬ ዳኜ ስለፊስቱላ በማስተማርም ሆነ ህመምተኞችን እያፈላለጉ ወደ ህክምና በመላክ ምን ያህል እንደተሳካላትና ምን ዓይነት ፈተናዎች እንደገጠሟት አጫውታናለች፡፡

‹‹መጀመሪያ 4 የፌስቱላ ህመምተኞችን አገኘሁ፡፡ ለዞን የአማራ ሴቶች ማበር ጽ/ቤት ደወልኩና በምን ወጪ ወደ ህክምና እንደምወስዳቸው ጠየቅሁ፡፡ ‹የሴቶች ማህበሩ ገንዘብ በእጅሽ ካለ ወጪ አድርገሽ በሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ወደ ባሕር ዳር ውሰጃቸውና ሒሳቡን አልማ ያወራርድልሻል› ተባልኩኝ፡፡

‹‹ይዣቸው ስሄድ ብዙ ሰቀቃ ደርሶብኛል፡፡ ተሳፍረን በሞጣ በኩል ስንሄድ አቢያ የሚባለው በረሃ ላይ ስንደርስ ቀትር ነበር፡፡ የበረሃው ኃይለኛ ሙቀት ከመኪናው ግለት ጋር ተጨምሮ በጣም እንደሚፋጅ እሳት ሆነ፡፡ በዚህም የህመምተኞቹ ጠረን ከልክ በላይ ገነነ፡፡ ተሳፋሪዎች ‹የሚሸተው ነገር ይውጣልን፣ ካልሆነም እኛ እንውጣ፣ የከፈልነው ገንዘብ ይመለስልን› አሉ፡፡ መኪናው ቆመ፡፡ ተሳፋሪዎች ህመምተኞቹን እናስወርዳለን አሉ፡፡ አለቀስኩኝ፡፡ ሾፌሩ ‹‹ለምን ታለቅሻለሽ›› ብሎ ጠየቀኝ፡፡ የፊስቱላ ህመምተኞች መሆናቸውንና የችግሩን ምንነት አስረዳሁት፡፡ ከተሳፋሪዎች ለተወሰኑትም ችግሩን በዝርዝር አስረዳኋቸው፡፡ ለሁሉም የነገርኳቸው በሚያሳዝን ሁኔታ ነው፡፡ ‹‹ሹፌሩ የሚረጭ ነገር እየረጨ ሽታውን እያስወገደ፣ እንደገና ሽታ ሲፈጠር እየረጨ ባሕር ዳር ደረስን፡፡ ለሚረጨው ነገር 13 ብር ከፈልኩት፡፡

‹‹ሾፌሩ በታክሲ እንድሄድ ቢነግረኝም፣ ባሕር ዳርን ከዚያ በፊት ስለማላውቀው የታክሲውን ለራሱ ከፍዬው እንዲወስደን ለመንኩት፡፡ ሆስፒታል አደረሰን፡፡ የሆስፒታሉን የስልክ ቁጥር ሰጥቼውም ደወለልኝና ዘበኛ ከፍቶልኝ ህመምተኞቹን አስረከብኩ፡፡ ሃኪሙም ስለህመሙና ህመምተኞችን እንዴት አፈላልጌ ማግኘት እንደሚቻል አስረዳኝ፡፡ የደረሰብኝን ሰቀቃ ነገርኩት፡፡ በመድረሴ ደስ ብሎኝም አለቀስኩኝ፡፡

‹‹ሃኪሙ ወቀሰኛል፡፡ መጀመሪያ ራሴን መጠበቅ እንዳለብኝና ለአልማ ብደውል መኪና ይልክልን እንደነበር ነገረኝ፡፡ ይህ ባይሆንም ለወረዳው መስተዳድር ትብብር መጠየቅ እንደነበረብኝ ካሳሰበኝ በኋላ፣ ‹‹በገጠመሽ ስቃይ ምክንያት ይህን መልካም ነገር ከመፈፀም እንዳትቀጠቢ›› አለኝ፡፡

‹‹ልጆቹን ለሆስፒታል ካስረከብኩኝ በኋላ በመኪና ወደ አልማ ጽ/ቤት ላከኝ፡፡ ከአልማ ሰዎች ጋር ተዋወቅን፡፡ አልማ ያወጣሁትን ወጪ በሙሉ አወራረደልኝ፡፡ ለመመለሻ የሚሆነኝን ወጪ በሙሉም ሰጠኝ፡፡

‹‹ሌላ ጊዜም ሌሎች 3 ህመምተኞችን አገኘሁ፡፡ አንዷ ይርከም አያል ትባላለች፡፡ በቀጥታ ለአልማ ደውዬ ራሱ መኪና ልኮ አሳከማቸው፡፡ እኔ መሄድ አላስፈለገኝም፡፡

‹‹በዚህ ዓይነት ሁኔታ አፈላልጌ እያገኘኋቸው ወደ አልማ የላክኋቸውና አሳክሟቸው የተመለሱት በጠቅላላ 17 ናቸው፡፡ ሁሉም ድነውልኛል፡፡ ሳገኛቸው ሮጠው መጥተው ይስሙኛል፡፡ ለእኔም ሆነ ለአልማ ያላቸው ፍቅር የተለየ ነው፡፡ ‹ለሌሎች እህቶቻችንም ድረሱላቸው› ይሉኛል፡፡››

ትላንት - ቤዛ
ዛሬም - ቤዛ

ወሬው ትኩስ በነበረባቸው በ1990ዎቹ መጀመሪያዎች ኤች አይ ቪ ኤድስን እጅግ አስፈሪ አውሬ አድርገን ያልቀጠርነው ስንቶቻችን ነን? ብዙዎቻችን አይስጡት ቅፅል ሥም እየሰጠነው፣ ከተፈጥሮው በላይ አግንነን በራሳችን ላይም ሆነ በሌሎች ላይ ሽብር ነዝተንበታል፡፡ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የተገኘባቸውንና ‹ሊኖርባቸው ይችላል› ብለን በደፈና የገመትናቸውን ሰዎች ሁሉ የሰውነት ክብር እየነፈግናቸው ሸሽተናቸዋል፣ አግልለናቸዋል፡፡ በዚያን ጊዜ ራስን ለማወቅ መመርመርና ሌሎችም እንዲመረመሩ መምከር የማናስበውና የማንሞክረው ከተራራ የገዘፈ ፍርሃታችን ነበር፡፡

በድፍረት ተጋፍጠው ራሳቸውን ቤዛ ያደረጉ ጥቂቶች መኖራቸው ደግሞ ሌላው እውነታ ነው፡፡ በዚህም፣ ራሳቸውን ‹‹ቤዛ የወጣቶች ስነ ተዋልዶና ኪነ-ጥበብ ክበብ›› አሰኝተው በበጎ አርአያነታቸው አያሌዎችን ሊታደጉ የቻሉት በደቡብ ወሎ ዞን የኮምቦልቻ ከተማ ጥቂት ወጣቶች በግንባር ቀደም ምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

ቤዛዎች ዛሬም ድረስ ቤዛ ናቸው፡፡ በክበብ ጀምረው፣ ከዚያም ወደ ማህበር ተሸጋግረው፣ አሁን ደግሞ ተለቅ ላለ መንግሥታዊ ያልሆነ ግብረ ሰናይ ድርጅትነት በቅተዋል፡፡ እኛም ከቤዛዎች መካከል አራቱን አነጋግረናል፡፡ እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹ክበባችን ቤዛ የወጣቶች ስነ-ተዋልዶና ኪነ-ጥበብ የተመሠረተው በ1993 ዓ.ም ነበር፡፡ ኤች አይ ቪ ኤድስ በከፍተኛ ደረጃ በሚፈራበትና ጭራቅ ተደርጎ በሚወሰድበት በዚህ ጊዜ አምስት ወጣቶች ሆነን ‹‹ምን እናድርግ?›› የሚል ጥያቄ አነሳን፡፡ ይህን ጥያቄ ስናነሳ ከቅን ልቦናችንና ድፍረታችን በስተቀር ምንም ዓይነት የገንዘብም ሆነ የማቴሪያል አቅም አልነበረንም፡፡

‹‹በዚያን ጊዜ የኤች አይ ቪ ኤድስ ህመምተኞች ሆነው በየቤታቸው የተኙ ነበሩ፡፡ አብዛኞዎቹ ሴት አዳሪዎች ናቸው፡፡ ማንም ሳይነግረንና ሳይቀሰቅሰን፣ በራሳችን ተነሳሽነት ብቻ እነዚህን ህሙማን የመንከባከብ ሃላፊነት ልንሸከም ተስማማንና ሥራ ጀመርን፡፡ ለህሙማኑ ድጋፍ ማድረግ የጀመርነው ከየኪሳችን ገንዘብ እያዋጣን የፅዳትና የምግብ አግልግሎት በማቅረብ ነው፡፡

‹‹ከህመምተኞቹ እየደረስን መምጣታችንና ማገዛችን ግን በብዙዎች አልተወደደልንም፡፡ ከቤተሰብ፣ ከጓደኞችና ከአጠቃላይ ከህብረተሰቡ የሚደርስብን አሉታዊ ተፅእኖ ቀላል አልነበረም፡፡ ህብረተሰቡ እየተጠየፈ የሚርቃቸውንና የማይጠይቃቸውን የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽተኞች መቅረብና መጠየቅ ከጥፋት በላይ የሆነ ጥፋት ሆኖ ተቆጠረብን፡፡

‹‹ይህ በዚህ እንዳለ ከህመምተኞቹ አንዳንዶቹ ይሞቱብን ጀመር፡፡ ቀሪ ሕፃናት ልጆቻቸው ወላጅ አልባ መሆናቸው ደግሞ ተጨማሪ አንገብጋቢ ጉዳይ ሆነብን፡፡ ወላጅ አልባ ሕፃናቱን ለበጎ ፈቃደኛ አሳዳጊዎች ለመስጠት ብዙ ጥረት አድርገናል፡፡

‹‹በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን ‹መቅድም ኢትዮጵያ የተባለ የኤች አይ ቪ ኤድስ ህመምተኞችን የሚረዳ ድርጅት እንዳለ ሰማን፡፡ ከመቅድም ኢትዮጵያ እገዛ ማግኘት የሚቻለው ግን ህመምተኞቹ ተመርምረው የኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ መኖሩን የሚያረጋግጥ የሃኪም መረጃ ሲያቀርቡ ብቻ እንደሆነ ተረዳን፡፡ የኤች አይ ቪ ምርመራ ማድረግ ራሱም እጅግ የሚያሳፍርና የሚያስፈራ ሆኖ የሚታይበት ጊዜ ነበር፡፡ እኛ ግን የመመርመርን አስፈላጊነት ማስተማር እንዳለብን በማመን ራሳችንም ከእነሱ

አቶ ሰይድ አህመድ
የቤዛ ፖስቴሪቲ ኢትዮጵያ ልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ

ጋር አብረን ተመረመርን፡፡ የክበባችን ሥም ‹‹ቤዛ›› የተሰኘውም በዚህ ነው፡፡ በእኛ ቤዛነት እየተመረመሩ ቫይረሱ ያለባቸው መሆኑ እየተረጋገጠ በመቅድም ኢትዮጵያ እገዛ እንዲደረግላቸው ያደረግናቸውም ብዙ ናቸው፡፡

‹‹እኛ አብዛኞዎቹ በጣም ዘግይተው ያወቁትንና ያደረጉትን ቀድመን ልናውቅና ልናደረግ የቻልን ወጣቶች ነበርን፡፡ አምስት ሆነን ጀምረነው በሂደት ብዙ አባላት ልናፈራና ከነጋዴዎች፣ ከቤት እመቤቶች፣ ከመንግሥት ሠራተኞችና ከሌሎችም በርካታ ደጋፊዎች እንዲኖሩን ማድረግ ችለናል፡፡

ወይዘሮ የኔዓለም አሻግሬ
የቤዛ ፖስቴሪቲ ኢትዮጵያ ልማት ድርጅት የማህበረሰብ ሠራተኛና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ

‹‹ኮምቦልቻ ብዙ ፋብሪካዎች የሚገኙባት የኢንዱስትሪ ከተማ መሆኗ ይታወቃል፡፡ ይህም፣ በተለያዩ የንግድ ሥራዎችና በመንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋሞች ውስጥ ከሚሰራው የህብረተሰብ ክፍል በተጨማሪ በርካታ የፋብሪካና የቀን ሠራተኞች የሚኖሩባት ከተማ መሆኗን ያመለክታል፡፡ ከአዲስ አበባ፣ ከትግራይና ከጅቡቲ ወደብ የሚያገናኙ ሦስት ዋነኛ አውራ ጎዳናዎች የሚገናኙባት ማዕከላዊ ስፍራ በመሆኗ ደግሞ የብዙ የንግድ ተሽከርካሪዎች መተላለፊያና ማደሪያ ነች፡፡ በአጠቃላይ ብዙ ወጣቶች የሚኖሩባት፣ በርካታ ሾፌሮችና ነጋዴዎች የሚስተናገዱባት ከመሆኗ ጋር፣ ኮምቦልቻ በኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ከተማ ነበረች፡፡ ይህም ነው ሃላፊነት እንዲሰማንና በራሳችን ተነሳሽነት ቤዛ እንድንሆን ያነሳሳን፡፡

‹‹መጀመሪያ ላይ ሸክሙ ቢከብድብንም፣ የኋላ ኋላ ግን ውጤታማ ልንሆን ችለናል፡፡ ህመምተኞችንና ወላጅ አልባ ሕፃናትትን ከመንከባከብና ከመደገፍ በተጨማሪ፣ ወደተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ እየገባን ተከታታይ ትምህርት በመስጠታችን ትልቅ ግምት የሚሰጠው የአስተሳሰብ ለውጥ አምጥተናል፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ እኛ የቡና ጠጡ ፕሮግራም እያዘጋጀን እናቶችን በኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያ ማወያየት የጀመርነው ቀደም ብሎ ነው፡፡

‹‹በምርመራ በኩልም ቀዳሚ ያደረግነው ራሳችንን ነው፡፡ መጀመሪያ ምርመራ ያደረግነው 20 የክበባችን አባላት ነን፡፡ እኛ ነጋሪ ብቻ ሳንሆን ተግባሪም መሆን ነበረብን፡፡ እየተመረመርን እያሳየናቸው፤ ‹‹ተመርመሩ›› እያልን የነገርናቸው በጣም ብዙ ናቸው፡፡ የ23 የትራንስፖርት ድርጅቶች ሾፌሮች እንዲመረመሩ ማስተማራችንን በምሳሌነት መጥቀስ እችላለሁ፡፡ እያዩንና እየሰሙን ፈለጋችንን የተከተሉትም ጥቂት አይደሉም፡፡ በእርግጥ ጊዜው እንደዛሬው ያልተመቸ፣ ፍርሃትና እፍረት የነገሰበት፣ ከሳ ብሎ የታዬ ሰው ሁሉ በዓይነ ቁራኛ የሚታይበትና የሚገለልበት ጊዜ ነበር፡፡

‹‹ያኔ የምርመራ ውጤት የሚነገረው በሳምንት ነበር፡፡ ከተመረመሩ በኋላ ሳምንት ሙሉ በብርድ ልብስ ተሸፋፍነው ተኝተውና ምግብ ሳይበሉ የሚቆዩ ነበሩ፡፡ ስለሚተፋፈሩና ስለሚፈራሩ፣ ውጤት ለመቀበል የሚሄዱትም ተለያይተው ነው፡፡ ይህም ሁለት ነገሮችን ያመለክታል፡፡ ፍርሃትና ጥርጣሬያቸው የወቅቱን አስቸጋሪነት የሚያስታውስ ሲሆን፣ በፍርሃትና በጥርጣሬ ውስጥም ሆነው መመርመር መቻላቸው ደግሞ ቤዛ ክበባችን ፈተና በበዛበት ጊዜና ሁኔታም እምነት መፍጠር የቻለ ጠንካራ መሆኑን ያመለክታል፡፡

‹‹ዛሬ ላይ ሆነን ስናወጋው ቀላል መስሎ ሊታይ ይችላል፡፡ ህብረተሰቡ የሸሻቸውን የኤች አይ ቪ ኤድስ ህመምተኞች መቅረብና መንከባከብ፣ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ማገዝ፣ ስለመከላከያና መቆጣጠሪያዘዴዎች ማስተማር፣ እየተመረመሩ ለምርመራ መቀስቀስና ማስመርመር፣ ኮንዶም ማደልና የመሳሰሉት ሁሉ ጊዜው ከመጠን በላይ ያከበዳቸው ተግባሮች ነበሩ፡፡ እኛም እንደ ክበብ ሳይሆን እንደ አንድ ትልቅ ድርጅት ሆነን የተቀናጀ የኤድስ መከላከል ሥራ ነበር የምንሠራው፡፡››

//